# የሄፓታይተስ ቢ ፈጣን እውነታዎች

በ 2 ደቂቃ ወይም ከዚያ ባነሰ ጊዜ ውስጥ ማወቅ ያለብዎት ነገር በጠቅላላ!

## ሄፓታይተስ ቢ ምንድን ነው?

ሄፓታይተስ ቢ በአለም ላይ በጣም የተለመደ አስጊ የጉበት ኢንፌክሽን ነው። በሽታው የሚከሰተው በሄፓታይተስ ቢ ቫይረስ (HBV) ሲሆን የጉበት ሕዋሳትን የሚያጠቃ እና ወደ ሲሮሲስ (ጠባሳ)፣ የጉበት በሽታ ወይም የጉበት ካንሰርን የሚያስከትል ነው።

በአዋቂነት ጊዜያቸው በበሽታው የተያዙ አብዛኞቹ ጤናማ ሰዎች ኢንፌክሽኑን መቋቋም እና ቫይረሱን ከደማቸው ማጽዳት ይችላሉ። ይህ እስከ 6 ወር ድረስ ሊወስድ ይችላል፣ እና በዚህ ጊዜ ውስጥ በሽታ አስተላላፊ ናቸው። እንዳለመታደል ሆኖ፣ ጨቅላ ህጻናት እና ታዳጊ ልጆች ለHBV ተጋላጭ ከሆኑ ስር ለሰደደ (የእድሜ ልክ) ኢንፌክሽን የመጋለጥ እድላቸው ከፍተኛ ነው።

በግምት ከ 5-10% አዋቂዎች፣ ከ 30-50% ልጆች፣ እና 90% ህጻናት ቫይረሱን የመዋጋት አቅም የላቸውም እና ስር ለሰደደ ኢንፌክሽን ተጋላጭ ናቸው። ስር በሰደደ በሽታ የተጠቁ ሰዎች ቫይረሱን ወደ ሌሎች ሰዎች ማስተላለፍ ይችላሉ (ምንም ምልክት ባያሳዩም) እናም በቀጣይ ህይወታቸው በጉበት በሽታ እና በጉበት ካንሰር የመጠቃት እድላቸው ከፍ ያለ ነው።

ጥሩው ዜና ሄፓታይተስ ቢን በአስተማማኝ እና ውጤታማ ክትባት መከላከል ይቻላል። ስር ከሰደደ የሄፓታይተስ ቢ ቫይረስ ጋር ለሚኖሩ ሰዎችም እንዲሁ ሌሎች ውጤታማ ህክምናዎች አሉ።

## ሄፓታይተስ ቢ በቁጥሮች

**በአለም ውስጥ፦**

- 1.5 ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎች በበሽታው ይያዛሉ
- በአለም አቀፍ ደረጃ 296 ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎች ስር በሰደደ የሄፓታይተስ ቢ በሽታ ተጠቅተዋል
- በየአመቱ 820,000 ሰው - 1 ሰው በየ 30 ደቂቃው - እንደ ጉበት ካንሰር ባሉ የሄፓታይተስ ቢ ችግሮች ይሞታሉ

**በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ፦**

- ቢያንስ 20,000 አዲስ ሰዎች በበሽታው ይያዛሉ
- እስከ 2.4 ሚሊዮን የሚሆኑ አሜሪካውያን ስር በሰደደ የሄፓታይተስ ቢ በሽታ ተጠቂ ናቸው
- በሺዎች የሚቆጠሩ አሜሪካዊያን እንደ ጉበት ካንሰር ባሉ የሄፓታይተስ ቢ ችግሮች ይሞታሉ

## ሄፓታይተስ ቢን መከላከል ይቻላል?

አዎ! አስተማማኝ እና ውጤታማ ስለሆነው የሄፓታይተስ ቢ ክትባት ሃኪምዎን ያነጋግሩ እና ራስዎንም የሚወዷቸውንም ሰዎች ህይወት ይጠብቁ። Centers for Disease Control & Prevention (CDC፣ የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከል) ሁሉም ጨቅላ ህጻናት፣ ልጆች፣ እስከ 59 አመት የሆናቸው አዋቂዎች፣ እና እድሜያቸው 60 እና ከዚያ በላይ የሆናቸው በሄፓታይተስ ቢ ኢንፌክሽን የመያዝ እድላቸው ከፍተኛ የሆኑ አዋቂዎች እንዲከተቡ ይመከራል። ከአሜሪካ ውጪ፣ World Health Organization (የአለም ጤና ድርጅት) ሁሉም ጨቅላ ህጻናት፣ ልጆች፣ እድሜያቸው እስከ 18 አመት የሆኑ ጎረምሶች፣ እና ተጋላጭነታቸው ከፍተኛ የሆኑ አዋቂዎች ክትባቱን እንዲያገኙ ይመከራል። ያስታውሱ፣ ለእድሜ ልክ ጥበቃ ጥቂት ክትባቶች ብቻ ነው የሚያስፈልግዎት!

## ሄፓታይተስ ቢ የሚተላለፈው እንዴት ነው?

ሄፓታይተስ ቢ የሚተላለፈው በበሽታው በተያዘ ሰው ደም እና የሰውነት ፈሳሾች በኩል ነው። ይህም በቀጥታ የደም ለደም ንክኪ፣ ልቅ የሆነ የግብረ ስጋ ግንኙነት፣ ህጋዊ ያልሆነ አደንዛዥ እጽ መጠቀም፣ እና በእርግዝና ወይም በወሊድ ወቅት በበሽታው ከተያዘች ሴት ወደ ልጇ ሊተላለፍ ይችላል።

**ሄፓታይተስ ቢ የሚተላለፈው፡-**

- በበሽታው ከተያዘ ሰው ጋር ቀጥተኛ የደም ንክኪ
- ልቅ የሆነ የግብረ ስጋ ግንኙነት
- ቆሻሻ ወይም ያልተጸዱ መርፌዎች (በ IV መድሃኒት መጠቀም፣ በመርፌዎች መነቀስ/መበሳት)
- በበሽታው ከተያዘ ሰው ጋር መኖር
- በእርግዝና ወይም በወሊድ ወቅት በበሽታው የተያዘች እናት አዲስ ወደተወለደው ልጇ
- ምላጮችን፣ የጥርስ ቡርሾችን፣ የጥፍር መቁረጫዎችን፣ የጆሮ ጌጦችን ወይም የሰውነት ጌጣጌጦችን በበሽታው ከተያዘ ሰው ጋር መጋራት
- በበሽታው በተያዘ ሰው መነከስ
- በመንገድ ዳር የጥርስ ሃኪሞች፣ ሃኪሞች እና የጸጉር አስተካካዮች የሚጠቀሙባቸው ያልተጸዱ መሳሪያዎች

**ሄፓታይተስ ቢ የማይተላለፈው፡-**

- ጉንጭ ወይም ከንፈር መሳም
- ማሳል ወይም ማስነጠስ
- የተለመደ ንክኪ እንደ መተቃቀፍ፣ እጅ መያያዝ፣ እጆችን መጨባበጥ
- በበሽታው በተያዘ ሰው የተዘጋጀ ምግብ መመገብ ወይም በበሽታው ከተያዘ ሰው ጋር ምግብ መመገብ



## ለሄፓታይተስ ቢ በጣም ተጋላጭ ማን ነው?

- በ HBV ከተያዙ እናቶች የተወለዱ ልጆች
- ስር በሰደደ ቫይረስ ከተያዘ ሰው ጋር በቅርብ የቤተሰብ ንክኪ ግንኙነት የሚኖሩ ሰዎች
- HBV ከተስፋፋበት ሃገር የተወለዱ ልጆች
- ልቅ የሆነ የግብረስጋ ግንኙነት የሚያደርጉ ወይም በ 6 ወራት ጊዜ ውስጥ ከአንድ በላይ የጾታ ግንኙነት ጓደኛ ያላቸው ሰዎች
- በጾታዊ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች (STD) የተያዙ ሰዎች
- ከወንዶች ጋር የጾታዊ ግንኙነት የሚያደርጉ ወንዶች
- መርፌዎች እና ሲሪንጆችን የሚጋሩ ግለሰቦች
- የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች ወይም የድንገተኛ ጊዜ ምላሽ ሰጪዎች
- የኩላሊት እጥበት ላይ ያሉ ሰዎች
- እንደ እስር ቤት እና የቡድን ቤቶች ያሉ የተቋም ቦታዎች የሚኖሩ ወይም የሚሰሩ ግለሰቦች

## ተጨማሪ የሄፓታይተስ ቢ የመረጃ ምንጮች (በእንግሊዘኛ)

- Hepatitis B Foundation: http://www.hepb.org
- CDC Division of Viral Hepatitis (የቫይራል ሄፓታይተስ ክፍል)፡- https://www.cdc.gov/hepatitis/
- World Health Organization: http://www.who.int/mediacentre/factsheets/fs204/en/
- Immunization Action Coalition: http://www.immunize.org